የመጽሀፍ ዳሰሳ

ይህ ጽሁፍ የሚያተኩረው ለውጥ በተሰኘው መጽሀፍና በጥልቅ መልዕክቱ ዙሪያ ነው። የተጻፈው በኡስታዝ በድሩ ሁሴን ሲሆን የመጀመሪያ ህትመቱ በ 2009 ዓ.ል. ነው። ጠቅላላ የገጾቹ ብዛት 255 ሲሆን በ 9 ክፍሎችና በ 58 ንዑስ ክፍሎች የተጻፈ ምናባዊ መጽሀፍ ነው።

በመጽሀፉ ውስጥ ስለ ዕውቀት በዋነኝነትና በስፋት ተዳሷል። ዕውቀት ከአምላክ በቸርነቱ ለባርያዎቹ የተለገሰ ጸጋ ነው። ይህም በተለያዩ መንገዶች የሚገኝ ሲሆን አንዱ መንገድ ንባብ ነው። እውቀትን ለመፈለግ መንገድ የጀመረ አላህ የጀነትን መንገድ ያገራለታል። የእውቀት አይነቶች በነፍስ ወከፍ ወይም በተወሰኑ የማህበረሰብ ክፍሎች ብቻ የሚታወቁ ሊሆኑ ይችላሉ። የአንድ ህዝብ ከፍታው የሚለካው በእውቀትና በአንባቢ ብዛት ሲሆን አለዕውቀትና እዝነት መመራት ወደ ጥፋት ይወስዳል። ለዚህም ቀደምት የዕውቀት ባለቤቶችን አርአያ ማድረግና ሁለገብ ዕውቀትን መቅሰም አይነተኛ መፍትሄ ነው።

ሌላው የተነሳ ጉዳይ ስለ ንባብ ነው። አንብብ የሚለው መርህ በእስልምና ከውልደት እንስቶ በህይወት እንዲሁም ከሞትም በኋላ የሚታዘዙበት ስርአት ነው። እንደ ነፍስ ወከፍ ገቢ የነፍስ ወከፍ ንባብም የአንድን ሀገር እድገት ከሚያመላክቱት መለኪያዎች አንዱ ነው። ይህን ለማጠናከር የንባብ ክበቦችን ማስፋፋት፣ ቤተ መጻህፍትን ማቋቋምና ውይይቶችን ማድረግ ከግለሰብ አልፎ ማህበረሰብን ይቀይራል። አዕምሮ ለሰው ልጅ ትልቁ ስጦታው ሲሆን ክፋ ስሜትን ድል በመንሳት ለባለቤቱ ክብርን ያጎናጽፋል። ልክ እንቅስቃሴ የአካል ጡንቻዎች እንደሚያዳብረው ሁሉ የአዕምሮን ጡንቻዎች በንባብ በማዳበር የጠነከረና የላቀ አዕምሮ እስከ እርጅና ጊዜ ይዞ መቆየት ያስችላል።

የዕውቀት መምህር ለተማሪዎቹ ሊያካፍላቸው የሚችሉ ዕውቀቶች አንድ በአንድ ተነስተዋል። በመጀመሪያ ወጣቶችን በተቅዋና በተውበት አደራ ማለት ነው። በመቀጠል ስለ ረሱል (ሰ.ዐ.ወ) ውዴታና ክብራቸውን ስለመጠበቅም ተጨማሪ ማሳሰቢያ መስጠት ነው። ወሳኝ ከሆኑ ዕውቀቶች መሀከል ስለታሪክ ፍልስፍና፣ በእስልምና ስለ ዕምነት ነጻነት እንዲሁም ፍትህ በእስልምና ከዘር፣ ከቀለም፣ ከዕምነት፣ ወዘተ... በላይ መሆኑ ተወስቷል። ሌላው የሰው ልጅ የመፈጠር አላማዎች በሶስት ተከፍለው ቀርበዋል። እነዚህም የአምልኮ፣ በምድር ላይ ወኪልነትና ምድርን አሳማሪነት ናቸው።

ሌላው ወጣቶች የተመከሩበት ጉዳይ ሁሉም ነገር አላፊ መሆኑንና የተረጋጋ ህይወት እንዲመሩ ነው። ስለዝሙትና ስለመንገዶቹ አስከፊነት፣ ስለሰይጣን ውስወሳዎችና የኢማን መጠበቂያ መንገዶች ተወስቷል። የአኬራ ወዳጅነት ዘላቂ የሆነ፣ የአርሽን ጥላ የሚያስገኝና ከመጥፎ ተግባራት የሚጠብቅ መሆኑ ተገልጸል። ትዳርን በተመለከተ ሁለቱም ተጋቢዎች የሚጠበቅባቸውን በማሟላት፣ በቀረው በመደጋገፍና በመልካም ባህሪይ በመኗኗር ማሳለፍ አለባቸው። ከሁሉም ደግሞ ይቅር መባባል በግለሰብም ሆነ በማህበረሰብ ደረጃ ጎጂ አስተሳሰብን በማስወገድ ወደ እድገትና መረጋጋት የሚመራ ይሆናል።

ከራስ ጋር የጥሞና ጊዜ በማሳለፍ ክፍተትና ጥንካሬን ማወቅ፣ መፍትሄ ማበጀት አልፎ ተርፎ አካባቢ ላይ ያለን ተግዳሮት ወይም አመቺ ሁኔታ ማጥናት ያስችላል። በሰው ህይወት ሶስት አይነት አለሞች ሲኖሩ መሰረታዊውና የመጀመሪያው አለም የአስተሳሰብ አለም ነው። ለውጥ የሚጀምረውም ከዚሁ ነው። ይህ ሲስተካከል ቀሪዎቹ አለሞች ማለትም የግንኙነትና የምርት አለም እየተስተካከሉ ይሄዳሉ። ውጤታማ ለመሆን ሰበቦችን ማድረስ፣ መወሰንና ጽናት መኖር አስፈላጊ ናቸው። በህይወት ትልቁ ሽክም የሚሸከሙት ወይም የሚኖሩለት አላማ አለመኖር ነው። ሁሌም ተመሳሳይ ህይወት አሰልቺ በመሆኑ ከምኞት ቀጠና መውጣትና መስዋእት መክፈልም ሌላው ተቀዳሚ ተግባር ነው። እግረ መንገዳችንን የሚገጥሙንን አሉታዊና አዎንታዊ ሃይሎችን እያመጣጠንን በአግባቡ በመጠቀም ስኬታማ መሆን ይቻላል። የለውጥ መሰላሎች የአስተሳሰብ፣ ሃላፊነት የመውሰድ፣ ህመሙን የመቋቋም፣ የማሳመርና የማስቀጠል መሰላል ናቸው። በእነዚህ የእሴት መሰላሎች ስንወጣ በዋነኝነት

አምላክን የማስደሰት ተነሳሽነት ኖሮን በመቀጠል የላይኛው እርከን ላይ መልካም ባህሪያትን ዝቅተኛው እርከን ላይ ደግሞ ጎጂ ባህሪያትን በማድረግ ውጤታማ መሆን እንችላለን።

ጽሀፉ ሲጠቃለል መጽሀፍ ጥሩ ወዳጅ በመሆኑ ጊዜ፣ ሁኔታና ቦታ ሳይመርጥ አብሮ የሚሆን፤ ቢተውት የማይተው፣ እውቀት የሚያስጨብጥና ለችግሮች ሁሉ መፍትሄ የሚያበጅ ነው። እውቀትና የመጽሀፍ ንባብ ከወጣትነት ጀምሮ በአግባቡ ከተጠቀሙበት የአስተሳሰብን ለውጥ በማምጣት ግለሰብና ማህበረሰብን የሚቀይር ትልቅ የህይወት ስንቅ ነው። ለሌሎች በመኖር ለራስ መኖር በሚል መርህ ደግሞ የእውቀት ባለቤቶች ይህንን በጎ ተግባርና ዕውቀት በማስተላለፍ ስራው ቀጣይነት እንዲኖረው ማድረግ ይጠበቅባቸዋል።

በሰሚራ ፈድሉ ከድር

መጋቢት 2014 ዓ.ል.

እድሉ ስለተሰጠን እናመሰግናለን